

# የብሩሴሎሰስ ወይንም የውርጃ በሽታ

“የብሩሴሎሰስ በሽታ ከእንሰሳት ወደ እንሰሳት እና ከእንሰሳት ወደ ሰዎች ይተላለፋል፡፡”



ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA

ግብርና ሚኒስቴር MINISTRY OF AGRICULTURE

EFCC ETHIOPIA

USAID FROM THE AMERICAN PEOPLE

JOHNS HOPKINS Center for Communication Programs

## ሀ. የብሩሴሎስስ ወይንም የውርጃ በሽታ

በአይን የማይታዩ ረቂቅ ህዋሳት/ ባክቴሪያ አማካኝነት በዋናነት የእንስሳትን የመራቢያ አካላቸውን የሚያጠቃ ተላላፊ በሽታ ነው፡፡ የብሩሴሎሲስ በሽታ ከእንሰሳት ወደ እንሰሳት እና ከእንሰሳት ወደ ሰዎች ይተላለፋል፡፡ በሽታው በአብዛኛው በበጋ ወራት ይታያል፡፡

## ለ. የብሩሴሎስስ ወይንም የውርጃ ምልክቶች

### 1. በሰዎች ላይ

- በሽታው ሲከሰት እንደማንኛውም ትኩሳት አምጪ በሽታዎች እንደ፤
  - ለረዥም ቀናት የሚቆይ ትኩሳት
  - የድካም ስሜት
  - የምግብ ፍላጎት መቀነስ ያሉ ምልክቶችን ያሳያል፤

### 2. በእንስሳት ላይ

- ሴት/አንስት እንስሳት ላይ ተደጋጋሚ ማስወረድ ሲታይባቸው
- ወንዶቹ/ተባዕት ላይ ደግሞ የመራቢያ አካላት እብጠት ሊታይባቸው ይችላል።



## ሐ. የበሽታው አራት ዋና ዋና መተላለፊያ መንገዶች

1. በንክኪ ውርጃ ጋር የተያያዙ ፈሳሾች፤ ደም እና ሌሎች የውርጃው ቅሪቶች እንዲሁም የተበከለ አካባቢ (አፈርና ውሃ) ጋር የሚደርግ ጥንቃቄ የጎደለው ንክኪ
2. የሥራ ሁኔታ ተጋላጭነት፤ ከእንስሳት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ባላቸው ሙያዎች (እንሰሳት ማዋለድ፤ ወተት እና የወተት ውጤቶች) ማሰማራት
3. ወተት እና የወተት ተዋፅኦዎችን በአግባቡ ሳያበስሉ መመገብ
4. ከሰው ወደ ሰው፤ በደምና የደም ተዋፅኦ ልገሳ (ይህ መተላለፊያ መንገድ በጣም ዝቅተኛ አጋጣሚ ያለው የመተላለፊያ መንገድ ነው።)

## መ. መከላከያ መንገዶች

- ወተት እና የወተት ተዋፅኦዎችን በአግባቡ አፍልቶ ወይንም አብስሎ መመገብ ።
- እንሰሳትን በምናዋልድበት ወቅት እጃችንን፤ አፋችንን መሸፈን፤ ሌላው የሰውነት ክፍላችንም እንዳይነካካ ጥንቃቄ ማድረግ
- ከእንስሳት ጋር የምናደርገው ንክኪ ተገቢ የሆነ መከላከያ ባለው መልኩ እንዲሆን ማድረግ፥
- ካስወረዳት እንስሳ የሚወጣውን ማናቸውንም ነገሮች እንደ ደም እና ሌሎች ፈሳሽ ነገሮች አካባቢውን እንዳይበክሉ በደንብ ማፅዳት እና በጠንካራ ላስቲክ ጠቅልሎ መቅበር ወይንም ማቃጠል።
- ከውርጃው ወይንም ከፈሳሹ ጋር ንክኪ ያላቸውን ማናቸውም ነገሮች በተገቢው ሁኔታ ተዘፍዝፎ ማጠብ

## እንስሳት በብሩሴሎስስ በሽታ ሲታመሙ መወሰድ የሚገባቸው እርምጃዎች፤

- የበሽታው ምልክት/ ውርጃ የተከሰተባቸው እንሰሳት ሲታዩ ወዲያውኑ በአቅራቢያ ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ
- ያስወረዱ እንሰሳት ከሌሎች እንሰሳት ለይቶ ማሰር
- በዚህ በሽታ የተጠቁ እንሰሳትን ለሌሎች ሰዎች አሳልፎ አለመስጠት ወይንም አለመሸጥ

## ቁልፍ መልእክቶች፡-

- የብሩሴሎስስ በሽታው ከእንሰሳት ወደ እንሰሳት እና ከእንሰሳት ወደ ሰዎች የሚተላለፍ በሽታ ነው፡፡
- ወተት እና የወተት ተዋፅኦዎችን በአግባቡ አፍልቶ ወይንም አብስሎ መመገብ ከብሩሴሎስስ እና ሌሎች ተዛማጅ በሽታዎች ራስንና ቤተሰብን ለመጠበቅ ይረዳል፡፡
- በዚህ በሽታ የተጠቁ እንሰሳትን ለሌሎች ሰዎች አሳልፎ አለመስጠት ወይንም አለመሸጥ
- ያስወረዱ እንሰሳት ከሌሎች እንሰሳት ለይቶ ማሰር እና በአቅራቢያ ለሚገኝ የእንስሳት ጤና ባለሙያ ሪፖርት ማድረግ